የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፴
አዲስ አበባ ሰኔ ፳፪ ቀን ፲፱፻፺፰

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

12th Year No. 30
ADDIS ABABA 29th June, 2006

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፬፻፺፬/፲፱፻፺፰ ዓ.ም

የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ /ማሻሻያ/ አዋጅ … ገጽ ፫ሺ፬፻፳፪

CONTENTS

**Proclamation No. 494/2006**

Labour (Amendment) Proclamation…. Page 3422

**አዋጅ ቁጥር ፬፻፺፬/፲፱፻፺፰ ዓ.ም**

**የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅን ለማሻሻል**
**የወጣ አዋጅ**

የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር ፫፻፸፯/፲፱፻፺፮ን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ(፩) እና /፫/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ /ማሻሻያ/ አዋጅ ቁጥር ፬፻፺፬/፲፱፻፺፰ ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. ማሻሻያ

የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር ፫፻፸፯/፲፱፻፺፮ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፣

፩/ የአንቀጽ ፫ ንዑስ አንቀጽ ፪ ድንጋጌ /ሐ/ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ድንጋጌ /ሐ/ ተተክቷል።

## PROCLAMATION NO. 494/2006.

## A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE AMENDMENT OF THE LABOUR PROCLAMATION

**WHEREAS,** it has become necessary to amend the Labour Proclamation No. 377/2003;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Sub Articles (1) and (3) of Article 55 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows;

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Labour (Amendment) Proclamation No.494/2006."

**2. Amendment**

The Labour Proclamation No. 377/2003 is hereby amended as follows:

1/ The provision of (c) of Sub-Article 2 of Article 3 is deleted and replaced by new provision (c) of Sub-Article 2 of Article 3

"ሐ/ የሥራ መሪን ማለትም በሕግ ወይም እን ደድርጅቱ የሥራ ፀባይ በአሠሪው በተሰጠ የውክልና ሥልጣን መሠረት የሥራ አመራር ፖሊሲዎችን የማውጣትና የማስፈጸም ከነዚሁ በተጨማሪ ወይም እነዚህኑ ሳይጨምር ሠራ ተኛን የመቅጠር፣ የማዛወር፣ የማገድ፣ የማሰ ናበት፣ የመመደብ ወይም የሥነ-ሥርዓት እርምጃ የመውሰድ ተግባሮችን የሚያከናው ንና የሚወስን ግለሰብን የሚመለከት ሲሆን፣ እንዲሁም እነዚህን የሥራ አመራር ጉዳዮች አስመልክቶ የአሠሪውን ጥቅም ለመጠበቅ አሠሪው ሊወስድ ስለሚገባው እርምጃ በራሱ የውሳኔ ሀሳብ የሚያቀርብ የሕግ አገልግሎት ኃላፊውንም ይጨምራል::"

፪/ በአንቀጽ ፴፱ ንዑስ አንቀጽ ፩ ስር የሚከተሉት አዲስ ድንጋጌዎች /ሰ/፣ /ሸ/ እና /ቀ/ ተጨምረዋል፣

"ሰ/ የፕሮቪደንት ፈንድ ሽፋን ወይም የጡረታ መብት የሌለው ሲሆንና በጡረታ ሕግ የተመለከተው መደበኛ የጡረታ ዕድሜ ላይ ደርሶ ከሥራ ሲገለል፣

ሸ/ ቢያንስ አምስት ዓመት በአሠሪው ዘንድ የሥራ አገልግሎት ኖሮት በሕመም ወይም በሞት የሥራ ውሉ ሲቋረጥ ወይም ሥራው ላይ የሚያስቀይ ከሥልጠና ጋር የተያያዘ ለአሠሪው የውል ግዴታ ሳይኖር በት ሥራውን በገዛ ፈቃዱ ሲለቅ፣

ቀ/ በኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ሕመም ምክንያት በራሱ ጥያቄ የሥራ ውሉ ሲቋረጥ::"

፫/ የአንቀጽ ፩፻፴ ንዑስ አንቀጽ /፮/ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ /፮/ ተተክቷል፣

"፮/ ተደራዳሪ ወገኖች በሥራ ላይ ያለ የኅብ ረት ስምምነት ካላቸው፣ የተፈፃሚነቱ ዘመን ከማብቃቱ ከ፫ ወር በፊት የኅብረት ስምምነቱን ለማሻሻል ወይም በሌላ ለመ ተካት ተቀራርበው ድርድሩን ይጀምራሉ:: ሆኖም የኅብረት ስምምነቱ የሚጸናበት ጊዜ ካበቃበት ቀን ጀምሮ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ድርድሩ ፍጻሜ ካላገኘ ደመወ ዝንና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን የሚመለ ከቱት የሥራ ዘመኑ ያበቃው የኅብረት ስምምነት ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት አይኖ ራቸውም::"

"(c) managerial employee who is vested with powers to lay down and execute management policies by law or by delegation of the employer depending on the type of activities of the undertaking with or without the aforementioned powers an individual who is vested with the power to hire, transfer, suspend, lay off, assign or take disciplinary measures against employees and include legal service head who recommend measures to be taken by the employer regarding managerial issues by using his independent judgment in the interest of the employer;"

2/ The following new provisions (g), (h) and (i) are added to Sub-Article (1) of Article 39:

"g) where he has no entitlement to a provident fund or pension right and his contract of employment is terminated upon attainment of retirement age stipulated in the pension law;

h) where he has given service to the employer for a minimum of five years and his contract of employment is terminated because of his sickness or death or his contract of employment is terminated on his own initiative provided that he has no contractual obligation, relating to training, to serve more with the employer.

i) where is contract of employment is terminated on his own initiative because of HIV/AIDS.

3/ Sub-Article (6) of Article 130 is deleted and replaced by the following new Sub-Article (6):

"6) parties to a collective agreement shall commence negotiation to amend or replace their collective agreement within 3 months before the expiry date of the validity period of the collective agreement; provided, however, that if the negotiation is not finalized within 3 months from the expiry date of the collective agreement, the provisions of the collective agreement relating to wages and other benefits shall cease to be effective."

፬/ አንቀጽ ፩፻፹፭ ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፩፻ ፹፭ ተተክቷል፣

"፩፻፹፭ በማንኛውም ወገን ላይ ስለሚፈጸም ቅጣት

፩/ ማንኛውም አሠሪ፣ የሠራተኛ ማኅበር፣ ሠራተኛ ወይም አሠሪውን ወክሎ የሚሰራ ሰው፣

ሀ/ በዚህ አዋጅ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት በወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎች ስለሠራተኛ ደህንነት የተደነገጉትን በመተላለፍ የሠራተኞችን ሕይወት ወይም ጤንነት ለከባድ አደጋ የሚያጋልጥ ድርጊት የፈጸመ ወይም በዚህ አዋጅ ለሴት ሠራተኞች ወይም ለወጣት ሠራተኞች ሊደረግ ስለሚገባው ልዩ እንክብካቤ የተደነገጉትን የተላለፈ፣

ለ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፩፻፷ የተደነገገውን የተላለፈ፣

ሐ/ በዚህ አዋጅ ወይም በሌሎች ሕጎች ድንጋጌዎች መሠረት የሥራ ሁኔታ ተቆጣጣሪ የሚሰጠውን ትዕዛዝ ያላከበረ፣ ወይም

መ/ ኃላፊነት ለተሰጣቸው ባለሥልጣኖች ሆን ብሎ ትክክል ያልሆነ መረጃ ወይም መግለጫ የሰጠ፣

እስከ ብር ፩ሺ፪፻ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።

፪/ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፩፻፴ ንዑስ አንቀጽ /፪/ ወይም /፬/ የተመለከተውን ግዴታ የተላለፈ አሠሪ፣ የሠራተኛ ማኅበር፣ ሠራተኛ ወይም አሠሪውን ወክሎ የሚሰራ ሰው እስከ ብር ፲ሺ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።"

## ፫. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሰኔ ፳፪ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም.

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

4/ Article 185 is deleted and replaced by the following new Article 185:

"185. Common offences

1/ An employer, a trade union, a worker or representative of employer which:

a) violates the provisions of this Proclamation or regulations or directives issued hereunder relating to the safety of workers and commit an act which expose the life or health of a worker to a serious danger, or does not give special protection to women workers or young workers as provided for in this Proclamation;

b) contravenes the provisions of Article 160 of this Proclamation;

c) does not comply with the order given by a labour inspector in accordance with this Proclamation or the provisions of other laws; or

d) gives intentionally false information or explanations to the competent authorities;

shall be liable to a fine not exceeding Birr 1,200

2/ An employer, a trade union, a worker or representative of employer which contra-~ venes Sub-Article (2) or (4) of Article 130 of this Proclamation shall be liable to a fine not exceeding Birr 10,000

## 3. Effective Date

This Proclamation shall enter into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 29th day of June 2006**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**